# እረጎበዝ፡ ምን ይሻላል?

ከማተቤ መለሰ ተሰማ፡

ባለፈው ሀምሌ ወር፡ ኢጋማሽ ላይ የአማራውን ሕዝብ፡ እልቂትና ፍልሠት፡ በተመለከተ የምን 2.4 ብቻ በሚል እርዕሥ ያቀረብሁትን፡ ጽሁፍ ሥደመድም ፡ እረጎበዝ ምን ይሻላል የሚል ጥያቄ በማንሣት ነበር፡ የተውሁት ምክናያቴም፡ የግል አሥተያይቴን ከማሥፈሬ በፊት( የነገር ወለምታ ሀኪሙ የአዋቂዎች ምክር ነው) እንደሚባለው ሁሉ፡ ከእኔ የተሻለ እውቀቱም ሆነ ብቃቱ ያላቸው፡ ኢትዮጵያውያን የሚሰነዝሩት፡ አሥተያይትና የሚለግሱት ምክር ካለ ላለመዘጋት፡ ፈልጌ እንጅ አንጠልጥየው ለመቅረት፡ ሥለአልሆነ ዛሪ በዚች ጽሁፍ፡ የምን ይሻላል ጥያቄይን፡ እንደገና እንዳነሣ ይህሌናና የመንፈሥ ጉልበቶቸ ተጋግዘው አዘውኛል።

በተንጠልጠል ወደቆየው፡ ሐሣብ ከመግባቴ በፊት ግን፡ የአማራውን ሕዝብ፡ ፍልሰት እንዴትነት፡ ያሣይ ይሆናል ብየ ሥለምገምት አንድ ተፈናቃይ ጎልማሣ አርሶ አደር፡ ከነገረኝ መካከል ጥቂቱን፡ እዚህ ላይ ላሰፍረው ወደድሁ፡ የዛሪ 4 አመት ገደማ ነው ወደ ጅጅጋ ከተማ ሔጀ ነበር፡ አካባቢውን አስቅድሜ አውቀዋለሁና፡ ድሮ የጉልበት ሰራተኛ ሲፈለግ፡ ለመጥራት አማል፣ አማል ተብሎ ነበር ያኔ ግን ሐበሺ፣ ሐበሺ በሚል ተተክቶ አገኘሁት፡ እኔ እስከማውቀው ድረሥ ሐበሺ ማለት፡ የአካባቢው ነዋሪ ሦማሌዎች፡ ሌላውን መጤ ብለው የሚያስቡትን የማዕል ሀገር ሰው፡ የሚጠሩበት ለዚያውም (የምጽት) አንደምታ ያለው ቃል ነበርና፡ ገርሞኝ ሣጠያይቅ፡ አማል እዚያው አካባቢ ለኖረው ወዛደር መጠሬያ ሲሆን፡ ሐበሺ ደግሞ ከማዕል ሀገር የእርሻ ሥራውን ጥሎ ለተሰደደው፡ ሕዝብ የተሰጠ ሥም ነው፡ እና አማሎች የሚሰሩት፡ ተከራክረው በውድ ዋጋ ሲሆን፡ ሐበሾች ግን ሥሩ የተባሉተን ሁሉ ያለማቅማማት፡ ሲሰሩ ውለው፡ ሣይከራከሩ፡ የተሰጣቸውን ብቻ ተቀብለው፡ በማመሥገን ነው የሚሄዱት፡ ተባልሁ። ነገሩ ከነከነኝና ከተማውን ካጥለቀለቀው፡ የወያኔ የክፋት ሥራ፡ መሿዕት በቅየው ሲኖር ኩሩ የነበረ አርሦአደርና፡ ዛሪ እንደ መገልገያ ዕቃ ከሚቆጠረውና ሐበሺ እየተባለ ከሚጠራው፡ መካከል በዕድሜ ጠና ያለውን በመምረጥ፡ ጠቀስሁና ሻይ ቡና እያልን ወጋችንን ስንቀጥል፡ ለምን እንደዚህ በገፍ እንደተሰደዱ፡ እንዲነግረኝ ጥያቄየን በለሆሣሥ አቀረብሁለት፡ በመጀመሪያ የመንግስት ሰለይ፡ መሥየው አገረገር፡ በኋላ ግን አለመሆኔን ለመግለጽ ያደረግሁት፡ ጥረት ተሣካልኝ መሰል፡ በፊቱ ከባድ የሀዘን ድባብ አጥልቶ፡ ታሪኩን እንዲህ ሲል አወጋኝ፡ (ሥሜ ቅድም እንደነገርኩህ ስንተዋውቅ ማለቱ ነው፡ ሥጦታው አባሆይ ይባላል፡ ሀገሪ ጎንደር ነበር እድሜየ ወደ 55 አመት ሣይደርሥ አይቅርም፡ እና በደርግ ዘመን የገበሪ ማህበር ተመራጭ ነበርሁ፡ የአሁኑ መንግሥት፡ አዳህሪ ቢሮክራት ነህ በማለት፡ ለም የሆነውን መሪቴን ወስዶ ለካድሪዎቹ በመሥጠት፡ ለእኔ ምንም የማያበቅል፡ ጥፍ መሬት ሰጠኝና፡ መሪቱ እህል እንደማያበቅል፡ እየታወቀ ደግሞ ማዳበሬያ በዱቤ ወሥጀ እንድዘራበት በመገደዴ፡ ወሰድሁ፡ በአመቱ እንኳን የማዳበሪያውን ዋጋ የዘሩንም የሚያክል ሣላመርት፡ ቀረሁና 2 በሮቸና 2 ላሞቸ ከነጥጆቻቸው፡ ተወስደው በሐራጅ ተሸጠው፡ እዳው ተከፈለ። እኔም በአይኔ አልቅሸ በእጀ አብሸ፡ ዝም አልሁና ቀሪ ከብቶቸን ሽጭ የልጆቸ ቀለብ በመግዛት፡ ተቀምጭ ሣለሁ፡ አሁንም በዚኸኛው አመትም ደግሞ ማዳበሪያ እንድዎሥድ ተጠየቅሁ፡ መሬቱ እህል ስለማያበቅል፡ ክርሞ የምከፍለው አላገኝምና አልወስድም የአምናውን ሁኔታ አይታችሁ የለም ወይ አልሁ፡ ብተወስድም ባትውስድም፡ በሥምህ የመጣ የመንግሥት ኮታ ሰለሆነ መክፈልህ አይቀርምና፡ ብትወሥድ ይሻልሀል ሲሉኝ ያሰኛችሁን አድርጉ እንጅ አልወሥድም፡ ብየ ቁርጡን በመናገር ከረምሁ፡ ጊዜው ሲደርሥ በአመቱ ማለትነው እንድከፍል ተጠየቅሁ፡ ባልወሰድሁት ማዳበሪያ፡ ዕዳ ልከፍል አይገባኝም፡ በማለት ለወረዳ፣ ለዞን፣ ለክልል፡ አስተዳደር፡ አቤት ብል ሰሚአጣሁና፡ በመጨረሻ ከብቶቸ ተሸጠው ስለአልቁ፡ የቀሩኝን በጎቸና፡ ፍየሎቸ አህያ ሣይቀር ወሥደው፡ በሀራጅ በመሸጥ የማዳበሪያውን ዋጋ ሊያሟላ አልቻለም፡ በማለት ተመልሰው መጥተው፡ በላየላይ ቤቴን አፍርሰው፡ የቆርቆሮ ክዳኑን ሲወስዱት፡ ዛሪ የት እንደወደቁ የማላቃቸውን፡ ያለ እኔ ምንም ከእጅ ወደአፍ የሚሉበት፡ መተዳደሪያ የሌላቸውን፡ ሚሥቴንና ለመብል ያላነሱ ለሥራ ያልደረሱ 5 ልጆቸን፡ ጣራ ከሌለው ቤት ውስጥ ለርሀብ፣ ለጥም፣ ለዝናብና ለጸሀይ፡ ትቻቸው እያለቀሥሁ ማንነቴ ወደ ማይታወቅበት፡ ሀገር በመሰደድ እየው እዚህ፡ የመሞቻ ቀኔን እጠባበቃለሁ፡ ይህ የምታየው ሁሉ፡ ቁምጣና ጎጃም አዘነ የለበሰው ሰው በሙሉ፡ እንደእኔው፡ ከአማራው ክልል መሪቱን እየተነጠቀ ንብረቱ በማዳበርያ ዕዳ ተሸጦ እያለቅ የተሰደደ ነው። ሀገር ቤት የቀረው፡ የመንግስት ባለሚሉ ብቻ ነው፡ እነሱ የቻሉተን ያክል ለም መሬት ተመርጦ ይሰጣቸዋል፣ አቅራቢው የትግራይ፡ ልማት ማህበር ነውና፡ እንዳይከሥር፡ በግዳጅ ማዳበሪያ ውሰዱ አይባሉም እንደኛ ከብቶቻችሁን ቤታችሁ ውሥጥ አሥራችሁ ቀልቡ እንጅ ወደመስክ አታሠማሩ አይባልሉም፡ ሁሉም ነገር፡ የሞላላቸው ናቸው እኛ ግን፡ እግዚያብሔርም ከመንግስት ጋር አድሞብናል መሰል፡ የተሻለ እናገኛለን ብለን ብንሰደድ፡ እዚህም የገጠመን፡ ሞትን ሺሺት ቢሄድ ከማይቀበርበት ደረሰ፡ የተባለው ብሂል ነው፡ ስንቱ መሰለህ፡ እዚህ በእራብ፣ በወባና በውሣ ወለድ በሽታ፡ በእየቀኑ እንደቅጠል የሚረግፈው፡ ስንሞት የአካባቢው ነዋሪ ሦማሌዎቹን ማለቱነው፡ ሰውነው ካርቶን፡ የሞተው ይላሉ፡ ካርቶኖች እንግዴህ፡ እኛነን፡ በመኪና አውቀው ይገጩናል አይከሰሱም፡ በዚህ ላይ ትልቁ ድሀ ተንሹን ድሀ አይወደውም፡ እንደሚባለው፡ ሁሉ አማሎች አይወዱንም፡ ይደበድቡናል፣ የሰራንባትን ገንዝብ ይቀሙናል፣ እስከመግደልም ደርሰዋል፡ ተባብረን ለመከላከል ስንሞክር፡ ፓሊስ የሚያግዘው፡ እነሱን ነው ለአስተዳደር ስናመለክት፡ ለምን መጣችሁ አሁንም በአስቸኳይ፡ ወደየመጣችሁበት ሀገር ተመለሱ፡ ይለናል እንዳንመለስ ደግሞ መግቢያ የሌለን ከመሆኑም በላይ፡ መንግሥትም ከየትኛው ወንበዴ ጋር ከረማችሁ፡ አሁንሥ ምን ግዳጅ ተቀብላችሁ ነው የመጣችሁ፡ አውጡ በማለት አስቃይቶ ሥለሚገድለን፡ ለሞት ሞት እዚሁ ቁጭ ብለን መቸ እንድሚመጣ፡ መጠባበቁን መረጥን)፡ ነበር ያለኝ እባው እየተናነው። የእኔ እባም ሣላስበው፡ ፈንቅሎኝ በመውረዱ ሣለቅስ ሆቴል ውሥጥ ያለው፡ ሰው እንዳያየኝ በቅጥ እንኳን ደህና እደር ሣልለው ተለይቻው፡ ከያዝሁት ቤርጎ በመግባት፡ እልህ፣ ሀዘን፣ ቁጭት ምን ልለው እንደምችል ባልገባኝ ስሜት ውስጥ ገብቸ ሙሉ ሌሊት፡ አልጋው

እሥኪጠብበኝ ሥወራጭ፡ እንቅልፍ ሣልተኛ አደርሁ፡፡ ያሣያችሁ ክቡራን አንባብያን፡ እንደ ዶሮ ከጉልበቱ በላይ ለብሶ፡ ያለጫማ የሚኳትን አርሦ አደር አድሀሪ ቢሮክራት ሲባል፡ እንግዴህ ይህ የሆነው ከዛሪ 4 አመት በፊት ነው፡ አሁን ደግሞ፡ ሁሉም ነገር ከእለት ወደ እለት እየካፋ ሥለሆነ፡ የሔደው ዛሪ ያ ህዝብ ምን አይነት እልቂት ላይ እንደሚገኝ፡ መገመት አያዳግትም፡ እና ውድ አንባብያን አያሣዝንም? አያንገበግብም? በእውነት ሀገሩን ለሚወድ፣ ወገኑን ለሚያከብር፡ ዜጋ ሁሉ ቀን እረፍት፣ ሌት እንቅልፍ የሚነሣ አይሆንምን? ይህ ብቻ አይደለም ትንሽ ወደኋላ መለሥ ብለን፡ ለማያት ብንሞክር የአማራው ክልል ባለሥልጣናት፡ ከላይ በተገለጸው የማፈናቀያ፡ ዘዴ ተጠቅመው፡ አርሶ አደሩን ያለርሕራሔ፡ ሲያሰቃዩት በ1993 ዓ/ም ህግና መንግሥት አለ መሥሎት፡ አዲስ አበባ ድረሥ በመጓዝ፡ አራዳ ጊዮርጊስ ቤተክርሥቲያን አካባቢ ሰፍሮ የሌሊት ቁርና የቀን ሐሩር እየተፈራረቀበት፡ አቤቱታ ቢያቀርብ ያገኘው መልሥ ግድያ፣ እሥራትና ድብደባ ነው፡ በዚህ ወቅት ለአቤቱታ እንደወጡ፡ በወያኔ አፋኝ ቡድን ተወሰደው፡ የደረሱበት ያልታወቁ፡ ብዙናቸው ከዚያ የተረፈው፡ ሕይወቱን ለማቆየት ሲል ተወለዶ ያደገበትን ቅየ ጥሎ በመሰደድ፡ ወለጋ ሔዶ ጦም አደር መሪት በመፈለግ ሰፍሮ መኖር ሰጀምር አሁንም የወያኔ ካድሪዎች፡ በአካባቢው የሚኖረውን የኦሮሞኛ ቋንቋ ተናጋሪ ኢትዮጵያውያን፡ ወራሪ ጠላት የመጣበት አስመስለው በመቀስቀሥ፡ ከአማራው ክልል ሔዶ በሰፈረው ሕዝብ ላይ፡ ጦርነት እንዲከፍት በማድረጋቸው፡ ከግራ ከቀኝ እጅግ በጣም በርካታ ሕዝብ አልቋል፡ ሁለት ወፍ በአንድ ጠጠር እንዲሉ፡ እጅግ በጣም የሚፈሩትና የሚጠሉትን፡ የአማረኛና የኦሮሞኛ ቋንቋ ተናጋሪ፡ ወንድማማች ሕዝብ እርስ በእርሥ አፋጅተውታል። ከዚያ እልቂት የተረፈውና፡ ወደ 6000 የሚገመተው፡ ሕዝብ ምንም ጥሪት ሣያንጠለጥል፡ ሚስት የባሏን፣ ባል የሚስቱን፡ ወይንም እናትና አባት የልጃቸውን፡ እሪሣ እየተራመዱ፡ አባይን ተሻግረው፡ ምእራብ ጎምጃም ዞን ቡሪ ከተማላይ ሲሰፍሩ፡ ሀላፊነት የነበረበት የመንግሥት ተቋማት ዞር ብሎ አላያቸውም፡ ብቻ ሣይሆን፡ እንዲያውም፡ ግብረሰናይ፡ ድርጅቶች የሚሰጡት እርዳታ፡ ፈጥኖ እንዳይደርሥ፡ ቢሮክራሲያዊ መሰናክሎችን እየፍጠረ፡ መዳን የሚችለው፡ ብዙ ቁስለኛ እንዲሞት አድርጓል ። እና ለወደፊቱስ ምንድን ነው የሚሻለው ጎበዝ?!!! ከአሁን በኋላ እንኳን ለምንድን ነው? በአንድ ሰው ዕድሜ፡ በሚለካው የትግል ተሞክሮአችን፡ ከጥፋት በቀር ልማት እንዳለመጣልን እያወቅን፡ የተናጠል ትግልና የተቃዋሚ ተቃዋሚነትን፡ ሙጭጭ ብለን የምንይዘው!! ለምንድን ነው? በጋራ ችግራችንና በብሄራዊ ጉዳያች፡ ላይ በግልጽና በፍጹም ቅንነት በመቅራረብ ተነጋግረን፡ ከመጥፋታችን በፊት፡ የተባበረ ሐይላችንን፡ ወደጋራ ጠላታችን ለማዞር የማንሞክረው!! ለምንድን ነው? እሥካሁን ባራመድነው አቋምና፡ ባፈሰሥነው ሀቅም ያገኘነው ፋይዳ ምንድን ነው፡ በማለት አንድ ቦታላይ፡ ቆም ብለን እራሣችንንና የሀገራችንን፡ ተጨባጭ ሁኔታ በመገምገም፡ ሀገርን ከጥፋት ህዝብን ከዕልቂት፡ ለማዳን አቋራጭና አማራጭ የሆነውን፡ የጋራ ትግል ሥልት የማንነድፈው!! እንዲህ እንደሰናውር ግንበኞች፡ በሀሣብ እየተለያየን፣ በአመለካከት እየተራራቅን፡ ወያኔ እንደ ጠቦት በግ እየጎተተ አርዶ ይጨርሰን? በእኛ ድርሻስ ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር ከዓለም ካርታ ትፋቅ? እረጎበዝ ምንይሻላል?!!!

(የከፋው ሲያለቅሥ ደስ ያለው ሲዘፍን፡ ያለው ሞልቶት ሲያፈስ የሌለው ሲለምን) እንዳሉት ደራሲ ክቡር ዶ/ር ሐዲስ ዓለማየሁ እስከመቸ ነው ወገናችን በበቀል በትር፡ እንዲህ ሲቀጠቀጥና ወያኔ በሕዝብ እባ አስረሽ ምችው ሲል፡ ዝም ብለን የምናየው። አንድ ሕዝብ እንደሕዝብ፡ በሌላው መታፈርና መከበርን የሚቀዳጀው እኮ፡ በእውቀቱ፣ በስልቱና በሐይሉ እራሱን የሚችል፡ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው፡ ዛሪ በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ህዝብ፡ በተለይ ደግሞ የአማረኛ ቋንቋ፡ ተናጋሪውን በወያኔው ጎራ እንዲህ ያስናቀውና ያስደቀደቀው፡ የበይዎች አለመሰማማት ለተበይዎች ይበጃል፡ እንደሚባለው ፡ የእኛ በጋራ አለመቆምና ሀገርን ከጥፋት ወገንን ከእልቂት፡ ለማዳን በሁሉም ዘርፍ ካለው እምቅ ሓይል ላይ ጥቂቱን እንኳን ቆንጥረን ለመጠቀም ባለመሞከራችን፡ እንሆ መናቅ ብቻ ሣይሆን፡ ያህያ ደግ ዋጋው ከባድ ጭነት ነው፡ እንደሚባለው፡ በወገናቸን ላይ የሥቃይና የመከራው ቀንበር፡ ከመቸውም ጊዜ በካፋ ሁኔታ ከብዶ መሸከም ተስኖት፡ የህይወት መንኮራኩር ዋና ነዳጅ የሆነው ተስፋው ተሟጥጦ በማለቁ፡ በ 4 ቱም ማህዘን ወደስደት በመትመም፡ ካሰበው ሣይደርስና ምኞቱ ሣይሣካ፡ በእየበርሀው እየወደቀ፡ የዱር አራዊት ቀለብ ፡ በእየ እውቅያኖሱ እየጠለቀ፡ የባህር እንስሣት ምግብ፡ እየሆነና ለዚህ ሞራላዊ ድፍረቱም ሆነ አካላዊ ብቃቱ፡ ያልፈቀደለት እንደ እነ አቶ ሥጦታው፡ በገዛ ሀገሩ ላይ ባይታውር ጅሆተኛ ሆኖ ከእሪት የመረረ ህይወትን፡ እየተጋተ ነው ያለው፡ እና ጎበዝ ምን ይሻላል? እንደ እኔ ያለፈውን የማያስታውስ ለወደፊቱ እራይ አይኖረውምና፡ ያለፈውን ሣንረሣ በእየ ህሌና ጓዳችን በማስቀመጥ፡ ለወደፊቱ እስካሁን ሐገራችንን ከውድቀት፡ ህዝቧን ከውርድት፡ ያደረሰውን፡ ሰው ያቦካውን እኔ ካልጋገርሁ፣ ሰው የጋገረውን ደግሞ ቀድሜ እኔ ካልበላሁ፡ አይነትና እኔ ያልባረክሁት ነገር ሁሉ እርኩሥ ነው ፡ አባዚያችንን፡ አውልቀን በመጣልና በመካከላችን፡ የአላማና የግብ ልዩነት፡ ሣይኖር የሥልትን ልዩነት እንደትልቅ፡ እንቅፋት እየቆጠርን፡ መለያየታችንን ጨርሦ እንዲያከትም፡ በማድረግ የወያኔን እጅግ የረቀቀና መጠነሰፊ፡ የሀገርና የዘር ማጥፋት ዘመቻ ለመግታት ምን ማድረግ አለብን በሚለው ላይ፡ ሁሉም ትኩረት ሰጥቶ ክምር ሊረባረብና ከከንፈር መምጠጥ ባላፈ መሪት ላይ የሚታይ ተግባር ማከናወን፡ ይደር የማይባል፡ አቢይ ተግባር ሥለሆነ ከልብ ልንጋፈጠው ይገባል።

እውነቱን ለመናገር፡ አሁን ለእኛ ከወያኔ የበለጠ ጠላታችን፡ ፍርሀታችን፣ አለመተማመናችን፣ ከእኔ ወዲያ ላሣር ባይነታችን ናቸው። ከፉም ይሁን በጎ ምኞት፡ ጥቂትም ቢሆን እምነትና ቆራጥነት፣ ደጋፊነት፣ አሣታፊነት፣ ለጋራ አመራርና አሰራር ተገዥነት፡ ካልታከለበትና፡ በማናልብኝነት፣ በጥረጣሪና በፍርሀት፡ ከታጀለ እንደካሮት ቁልቁል ከማደግ የሚገታው፡ እንደሌለ የእኛ ትውልድ የአይን ምስክር ነው። ለማጠቃለል የማይቻልበት ምንም ምክናያት የለም እንጅ ካልተቻለም እንኳን ደጋፊም፣ ነቃፊም ባለበት መድረክ፡ ከሁለቱም ገለልተኛ የሚሆን ካለ፡ ለጊዜው እንደደጋፊ ይቆጠራል፡ ይባላልና በዚህ ወሣኝ ወቅት ጣልቃ እየገቡ የሌላውን የትግል ሞራልና ወቅታዊ እንቅስቃሴ፡ ከማሰናከልና ዓላማውንም ከማምከን፡ ለአንድነት በአንድነት መሰለፍ ካልተቻለምእኮ ማንንም ሣይነኩ፡ የእራሥን መንገድ መከተልም፡ ትልቅ ነገር ነውና እያንዳንዳችን፡ ሌላ ለማንም ብለን ሣይሆን ልትጠፋ ለተቃረበችው፡ ለምንወዳት ሀገራችንና፡ የስቃይ ህይወት በመግፋት ላይ ላለው ለምናከብረው ወገናችን፡ ሥንል ሁሉንም ትተን በጋራ በመሰለፍ፡ ከታች በህዝብ በመተፋቱ ሥሩ ተነቅሎ ከላይ የተንጠለጠለበት፡ የቡሽ አስተዳደር ቅርንጫፍ ተገንጥሎ፡ በማዕ

እንደውሀላይ ኩበት በደመነፍስ በመንሣፈፍ፡  ልጡ ተርሶ ጉድጓዱ ተምሶ  የተቀመጠውን፡ ይህነን ታሪክ አርካሽ፣ ሀገር ቆራሽና አሥውራሽ፡ የወያኔ ቡድን ግባተመሬት እናፋጥን፡ ጎበዝ በኢትዩጵያ አምላክ፡ እያልሁ ለዛሪን በምትከተለዋ የግጥም፡ ሥንኘ ልሰናበት።

## ምነው አቶ መለሥ

ግብሩ ሽያጭ ታክሱ ቫቱ ተመምሮ ፣
ፈጀው ህዝባዳሜን በጠቅላላ አክስሮ።
አቤት በአርሦ አደሩ የወረደው ፍዳ፣
ቁምሥቅሉን አሣጣው የማዳበሪያ ዕዳ።
ምነው አቶመለሥ አምላክን ቢፈሩ፣
የት ይድረሥ ነው የሚሉት አሁን አርሶ አደሩ።
በዚህ አውጫጭኙ ጉቦው መማለጃው ጣሪያ የደረሰ፣
በዚህ የዓመት ግብሩ ገቢን ያልዳሰሰ፣
የማዳበሪያ ህዳው ንብረቱ አሽጦ ቤቱን ያሥፈረሰ፣
የሚሆነው ሲያጣ ጥሎ ተሰደደ ልጁ እያለቀሰ።
ይማለዱት መለሥ በእግዜር እባክዎ፣
የማዳበሪያው ንግድ ከእንግዴህ ይብቃዎ።
ለሰሚው ግራ ነው በእውነት ያሥደንቃል፣
ነጋዴና መሪ በየት ታይቶ ያውቃል?
እረይገርማሉ!!!!!

ምነው አቶመለስ ትንሽ የሚራራ አንጀት የሌለዎት፣
ከሞሦሎኒ ጋር በምን እንለይዎት።
አሁን በቃ እንግዴህ ጌታው አቶ መለስ፣
ተሸክሟል ህዝቡ እሥከዛሪ ድረስ።
ብልጣብልጥነትን ይጠቀሟት ዛሪ፣
አበቃ ከእንግዴህ አይኖሩም በወሪ፡
አሁኑ ያምልጡ ብለው አውጭኝ እግሪ፣
አሁኑ ያምልጡ ብለው አውጭኝ እግሪ።

ነሐሴ ወር 2001
matebemelese@yahoo.com